# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 48 ሚያዚያ 8 2001 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

> ፖሊሶች ማንን እንደሚይዙና እንደሚያስሩ፣ ዳኞች በማን ላይ ምን አይነት ፍርድ ማስተላለፍ እንዳለባቸው በትእዛዝ ማስፈጸም እንዲችል አድርጎ ያቆመውን የአፈና ስርአት.... አይኑንን አፍጥጦ፣ ያውም በአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን፣ በአለም ህዝብ ፊት ሲናገር መለስ ዜናዊ የህሊና ጉንተላ የሚባል ነገር ፊቱ ላይ አይነበብም፡፡
>
> **ርዕሰ አንቀጽ**

## መለስ ዜናዊ በሚቀጥለው የይስሙላ ምርጫ የጠቅላይ ሚንስትርነቱን ቦታ እለቃለሁ ብሎ በሰጠው ቃል እንዳይጸና የወያኔ ኢህደግ ከፍተኛ ሃላፊዎች ልመና እንደጀመሩ ታወቀ።

ዘረኛና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የህዝብን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር እና የሚድያ ፍጆታ ለመሳብ ብሎ በሚቀጥለው ዙር ከጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ለመውረድ እፈልጋለሁ ማለቱ ይታወሳል። መለስ ስልጣኔን እለቃለሁ ማለቱን ማንም ጤነኛ ሰው ከምር ያልተቀበለው መሆኑ ቢታወቅም ከሰሞኑ በወያኔ ድርጅት ውስጥ የመለስን ውሳኔ ለማስለወጥ በሚል ሽርጉድ እንደበረከተ የግንቦት 7 ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ለማረጋገጥ ችሏል።

የግንቦት 7 ድምጽ ለጊዜው ስሙን ለመግለጽ በማይፈልገው አንድ ቱባ የወያኔ ባለስልጣን እንደተመራ በታወቀው የወያኔ ከፍተኛ አመራር ስብሰባ ላይ በሙሉ ድምጽ መለስ ቢያንስ እስከሚቀጥለው አምስት አመት በጠቅላይ ሚኒስትርነት መቆየት አለበት የሚል ውሳኔ እንደተላለፈም ደርሶበታል።

በዚሁ በቅርቡ ተደርጎ ነበር በተባለው ስብሰባ ላይ «ከእኛ መካከል የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ የሚመጥን የለም፤መለስ ከቦታው ከወረደ እና ሌላ ሰው ከተተካ ጉዳችን ይፈላል፤ ስልጣኔን እለቃለሁ የሚለውን አቋሙን በልመና ልናስቀይረው ይገባል...ወዘተ » የሚል ፍሬከርስኪ ድራማዎች ተደምጠው እንደነበር ከምንጮቻችን የደረሰን ዜና ጨምሮ አጋልጧል።

(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

## ወያኔ በመጪው ምርጫ አጃቢ ለማግኘት የሚያስችለውን አቋም በቅርቡ ይፋ ያደርጋል

በምርጫ 97 ዕርቃኑን የወጣውና የነጻ ምርጫ መኖር ሊያስከትልበት የሚችለውን መዘዝ የተረዳው የወያኔ ሥራ አስፈፃሚ በትናትናው ዕለት ባደረገው ስብሰባ፣ ባለፈው ዓመት በወረዳና የሚሚያ ምርጫ ወቅት የተከተለውን አሰራር መድገም በአለም አቀፍ ደረጃ ሊያስከትልበት የሚችለውን ነቀፌታ ከግምት ያስገባ ውይይት ካካሄደ ቦኋላ በምርጫ 2002 ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማሳተፍ የሚችል ነገር ግን እንደ ከዚህ በፊቱ ከቁጥጥር ወጥቶ ሥርዓቱን በውጪና በውስጥ ሊያሳጣ የሚችል እንዳይሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ የተሞላበት ስልት በአስቸኳይ ተነድፎ ሣራ ላይ እንዲዉል መወሰኑን ለአመራሩ ቅርበት ያላቸው የውስጥ ምንጮች ለግንቦት 7 ድምጽ ከላኩት መረጃ ለማወቅ ተችሎአል።

እንደዜና ምንጮቻችን መረጃ ለአገዛዙ ወገንተኛ ናቸው የሚባሉትንና ጽንፈኞች የሚላቸውን ለያይቶ ለየብቻ በማነጋገር አስቀድሞ ስምምነት በሚደረስባቸውና ወያኔ አብይ ናቸው በሚላቸው አጀንዳዎች ዙሪያ የምርጫው ጊዜ እየተቃረበ ሲመጣ በህዝብ ፊት ይፋ የአደባባይ ክርክር የማድረግ እቅድ በስትራቴጂው ውስጥ እንዲካተት ስምምነት ላይ ተደርሶአል።

(ወደገፅ 4 ዞሯል)

## መለስ ዜናዊ 5 የጦር ሄሊኮፕተሮችን ለዳርፉር የአፍሪካ ህብረት ጦር እንደሰጠ ታወቀ

በሰው ዘር ማጥፋት፤ በጦር ወንጀል እና ሰብአዊ ፍጡር ላይ ወንጀል በመፈጸም አለምአቀፍ ከበሬታ እና ተአማኝነት ባላቸው የሰብአዊ መብት እና የዘር ማጥፋት ወንጀል ተከላካይ ተቋማት የተከሰሰው የዘረኛው አምባገነን መለስ አገዛዝ፤ በዳርፉር ላለው የአፍሪካ ህብረት ጦር አምስት ሄሊኮፐተሮችን ከሰሞኑ እንደሰጠ የግንቦት 7 ወታደራዊ ምንጮች አጋለጡ።እንደወታደራዊ ምንጮቻችን ዘገባ የሄሊኮፕተሮቹ አሳልፎ መስጠት ብዙ ውዝግብ ያስነሳ ጉዳይ እንደነበር ታውቋል።አንዳንድ መኮንኖች የራሳችንን አየር ሀያል በቅጡ ሳናደራጅ እና በተራቡ ወገኖች ስም ተለምኖ በመጣ ገንዘብ የተገዛ ሄሊኮፕተር ለባእድ ሀገር መስጠት የለበትም ሲሉ መደመጣቸውን ወታደራዊ ምንጮቻችን ዘግበዋል።በጣም የሚገርመው አሉ ወታደራዊ ምንጮቻችን በጣም የሚገርመው ታላላቅ የሚባሉ የምእራብ ሀገራት ሄሊኮፕተር እንዲያዋጡ ተጠይቀው ዝምታን ሲመርጡ ወያኔ ተንደርድሮ የሀገርን ንብረት ለመስጠት መጣደፉ ነው ብለዋል።

ለአፍሪካ ህብረት የተሰጡት አምስት ሄሊኮፕተሮች ታክቲካል ሄሊኮፕተር የሚባሉ ሲሆኑ ዋጋቸው በጣም ውድ እና እቃ ከሚያመላልሱት ሄሊኮፕተሮች የተለዩ መሆናቸውን ወታደራዊ ምንጮቻችን ገልጸዋል።በሶማሊያ ገብቶበት ከነበረው የውልክና ጦርነት በተጨማሪ ወያኔ በርካታ ወታደሮቹን በዳርፉር ማስፈሩ በአፍሪካ ህብረት ስር ማስፈሩ ይታወቃል።

(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

## ታዋቂው የአሜሪካን አገር መጽሄት ኒውስ ዊክ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ክፉኛ የሚተች ጽሁፍ አወጣ፤ መለስ ባህሪውን እንዲያስተካክል ግፊት እንዲያደርግበትም ለባራክ ኦባማ አስተዳደር ጥሪ አቀረበ።

በዚህ ወር ለሚወጣው ጋዜጣ የተፃፈው ጽሁፍ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ አገር ውስጥ ለሚፈጽመው አፈና እና በሶማሊያ ላደረገው ግፍ ክፉኛ የሚተች ሲሆን፣ አሜሪካ ሽብርተኝነትን በመዋጋት ስም ለአገዛዙ እርዳታ የምትሰጠውን ያህል እንዳልተጠቀመች ተናግሯል።

ጽሁፉ፥ “ባለፈው ዓመት ብቻ፥ የመለስ ገዢ ፓርቲ ምርጫ ሰርቋል፣ ገለልተኛ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችን ከልክሏል፣ አፋኝ የፕሬስ ህግ አስተላልፏል፤ በኦጋዴን የተፈጸመውን ግፍ በተመለከተም ምርመራ እንዲያደርግ ጥሪዎች ተደርገውለት ቸል ብሎ አልፎታል” ሲል ወያኔ/ኢህአህአዴግን ተችቷል። ከ97ቱ ምርጫ በኋላ መለስ ተቃዋሚዎችን ማፈኑን በመጥቀስ፣ የቡሽ አስተዳደር ግን ከአልቃይዳ ጋር ንክኪ ያላቸውን የሶማሊያ ቡድኖች ይዋጋልናል ብሎ በዝምታ ከማለፉም በተጨማሪ ባለፈው የፈረንጆች ዓመት 1 ቢሊዮን ዶላር እርዳታ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መስጠቱን ዘግቧል።

እንደ ጋዜጣው ገለፃ፥ ምንም አንኳ የቡሽ አስተዳደር ወያኔ መራሹ መንግስት ለጸረ ሽብር ውጊያው አጋር እንደሆነ ቢናገርም፣ ያለው መረጃ ግን የሚያሳየው አሜሪካ የምትለግሰውን ገንዘብ ያህል ውለታ አለማግኘቷ ብቻ ሳይሆን፣ እግረመንገዷንም ጨካኝ አምባገነን እየደገፈች ነው። አምባገነኑ መለስ ሶማሊያ ገብቶ አይ.ሲ.ዩ. የተባለውን ቡድን በሁለት ሳምንት ውስጥ አባርሬያለሁ ከማለቱ አልሸባብ የተባለው የባሰ ቡድን ብቅ ብሏል በማለት ስለመለስ የሶማሊያ ዘመቻ ውድቀት ገልጿል። ጋዜጣው ጨምሮም፣ ምንም እንኳ ስዩም መስፍን እነዚህ ቡድኖች በጦር ደረጃ ድባቅ ተመተዋል ቢልም፣ አብዛኛውን ደቡብ ሶማሊያን ከመቆጣጠራቸው በተጨማሪ፣ ከአልቃይዳ ጋር ያላቸውን ትስስር አጠንክረዋል ብሏል።

(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

# በውሸት ተወልዶ በውሸት ያደገን ውሸት እንደሚገድለው ጥርጥር የለውም፡፡

የወያኔ ኢህአዴግ አዋላጅ ራሷ ወሸት ነበረች፡፡ ያሳደገችውም እራሷ ቅጥፈት ነበረች፡፡ አሁንም እየጎተተች ወደ ከርሰ መቃብሩ የምታንደረድረው ይህችው ውሸት ናት፡፡ ውሸቱ ሲጀምር እንዲህ ነበር፤ «ትግራይ በታሪኳ ገናና የነበረች አንድ ልኡላዊ ሃገር ናት፡፡ ትግላችን እራሳችንን ከኢትዮጵያ የቅኝ አገዛዝ ነጻ አውጥተን ነጻይቱን የትግራይ ሪፓብሊክ  መመስረት ነው፡፡»

የ1975ቱ ማኒፌስቶ በመባል የሚታወቀው የመለስ ዜናዊ ድርሰት አላማው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ለምንለው ሃቅ መሰረት በመሆን፣ በማጠናከርና በየግዜው የገጠሙትን ፈተናዎች አልፎ ለአንበት ዘመን እንዲበቃ ትግርኛ ተናጋሪው ህዝብ የከፈለውን ማለቂያ የሌለው መስዋእትነት በሃሰት ታሪክ ለመሰረዝ ነበር፡፡ የትግራዋይና የኢትዮጵያዊነትን የታሪክ ትስስር እንደ ደረቅ አጠና መተርተር ነበር፡፡ ገና ከመነሻው በቅጥፈት በተሞላ ልብ-ወለድ ታሪክ ላይ የዘርና የጥላቻ መርዝን መዝራት የፖለቲካው ፍልስፍና አድርጎ የተነሳው መለስ ዜናዊ በእዚህ ዘረኛ ጭፍን እምነቱ ታጥሮ የሁላችንም መጠለያ የሆነችውን ሃገር ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት ማየት እንዳይችል ታወረ፡፡

ወያኔ ‹የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው› በሚል መርህ የሚመራ እንደሆነ መላው ታሪኩ ይመሰክራል፡፡ በእዚህ ድርጅት ውስጥ ደግሞ በእንዲህ አይነቱ አሰራር የሰለጠነውና የገነነው ለረጅም ዘመን የወያኔ መሪና የድርጅቱ ርእዮተአለም አባት የሆነው መለስ ዜናዊ ነው፡ ከጥቂት አመታት በፊት የሊቢያ መንግስት ይፋ ባደረገው የሞሃመድ ጋዳፊ የቆየ ንግግር ላይ «መለስ ዜናዊ በእናቱ የመናዊ መሆኑን» እንደነገረው ጋዳፊ ለአዳማጮቹ በመግለጽ «ዜናዊ የሚለው ስሙስ፣ መልኩስ አረብ መሆኑን አያመለክትም ወይ» በማለት አድማጮቹን ሲጠይቅ እንደነበር ተዘግቦ አንብበናል፡፡ ይህ የመለስ ዜናዊን ማንነት ከሚያሳዩት በርካታ ምሳሌዎች አንዱ ነው፡፡

የ1984ቱ ረሃብ ሽፋን በማድረግ ወያኔ የውጭ መንግስታትንና አለም አቀፍ የግብረ ሰናይ ድርጅቶቹን በተወሳሰበ ማታለያ በሚለዮኖች የሚቆጥር ብር አጭበርብረው መለስና ጓደኞቹ የሚሊዮኖች ዶላሮች ጌታ መሆን እንደቻሉ እናውቃለን፡፡ ዛሬ አዜብ መስፍን እጅ የወደቀው የወያኔ የቢዝነስ ኢምፓየር የፋይናንስ መሰረቱ የተጣለው በእዚህ ገንዘብና ከኢትዮጵያ ህዝብ የተዘረፉ የእርሻ መሳሪያዎች፣ የጭነትና የህዝብ ማጓጓዛ መኪናዎችና ሌሎች ንብረቶች ሱዳን ውስጥ እየተቸበቸቡና በንግድ ስራ ላይ እየዋሉ የተከማች ነው፡፡ ወያኔ ስልጣን ከያዘ በኋላም በመጀመሪያ ጥቂት አመቶቹ ውስጥ ስልጣኑን በመጠቀም የሃገሪቱን የመከላከያና የፖሊስ በጀት ወደ ድርጅታዊ ካዝናው አዙሯል፡፡ ቀጥሎም እንዳሻው ከየባንኩ በብድር ስም በዘረፈው የኢትዮጵያ ህዝብ አንጡራ ሃብት ያካበተው ሃብት ገደብ የሌለው ሆኗል፡፡ ይህ ሁሉ የአደባበይ ሚስጥር ሆኖ በላበት ሁኔታ የአዜብ መስፍንና የመለስ ዜናዊ የግል ሃብት እየሆነ የመጣውን፣ ኤፈርት የተባለውን ታለቅ የቢዝነስ ተቋም የትግራይ ህዝብ በትግሉ ወቅት ባዋጣው ሃብት የቆመ ነው በማለት ላሞኛችሁ ሲለን መለስ ዜናዊ አያፍርም፡፡

ወያኔ ስልጣን ከመያዙ በፊትና በኋላም ከተለያዩ ቡድኖችና ድርጅቶች ጋር ያደረገው ግንኙነት ሸፍጥንና ተንኮል መሰረቱ ያደረገ ነበር፡፡ ዝርዝሩ የታሪክ ጸሃፊዎች እንጂ የጋዜጣ ርእስ አንቀጽ አዘጋጆች ሊሆን አይችልም፡፡ በተለይ ግን ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት፣ የመለስ ዜናዊ ሸፍጥ ከሌሎች ድርጅቶች አልፎ የገዛ ጓደኞቹንና የወያኔን አንጋፈ መሪዎች መብላቱ ነው፡፡

የማጭበርበርና የመዋሸት ባቡር ከደደቢት በረሃ አዲስ አበባ ከተማ፣ ያውም ምኒሊክ ቤተ መንግስት ያደረሰ፣ በተግባር የተፈተነ ስልት መሆኑ ታመነበት፡፡ «የትም ፍጪው ስልጣንና ጥቅሙን ግን አምጪው» የሚለውን የዱርዬ መርህ መለስ ዜናዊ የሃገር መሪ ከሆነም በኋላ ሊለቀው አልቻለም፡፡ ኢትዮጵያን የባህር መውጫ የሌላት ሃገር አድርጎ፣ ከኢትዮጵያ ደሃ ህዝብ ጉሮሮ እየተገፈፈ ለጅቡቲ በአመት ከአንድ ቢሊየን ዶላር በላይ የወደብ ግብር ከፋይ ያደረገን የክህደት ርምጃ መለስ ዜናዊ የራሱን ድርጅት አባላትና የኢትዮጵያን ህዝብ አጭበርብሮና ዋሽቶ ወሰነ፡፡

መለስ ዜናዊ ዘረኛነትን ለማሰፋፋት ህዝብን ከፋፍሎ ለመግዛት ይጠቅማል ብሎ ካሰበ ሃገርና ባንዲራ የሚባሉ ነገሮችን ለማንቋሸሽ ደንታ የለውም፡፡ መለስ ብሎ ግን የግል ንብረቱ ለሚቆጣጠረው የአልሜዳ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ስራ ለመፍጠር ሲፈልግ ደግሞ፣ ይህ ፋብሪካ በመንግስት ኪሳራ 300000 ባንዲራዎች እንዲያመርትና የባንዲራ ቀን በሃገሪቷ እንዲከበር መመሪያ ለመስጠት የማይቸግረው ጉደኛ ፍጥረት ነው፡፡

በመለስ ዜናዊ ቤት በአደባበይ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ብሎ፣ በውስጥ መመሪያ ተቃዋሚዎች በነጻነት እንዳይንቀሳቀሱ ማድረግ፤ ራሱ ምርጫን አጭበርብሮ፣ ስንጥር የሌላቸውን ተቃዋሚዎች ምርጫ አጭበረበሩ በማለት የስርአቱ ከፍተኛ ባለስልጣኖች በተሸነፉባቸው ቦታዎች በሙሉ ምርጫ እንዲደገም መወሰን ነውር አይደለም፡፡ የተጭበረበረን ምርጫ ህዝብ በጸጋ እንደማይቀበል፣ በእዚህ ህዝብም ላይ እንዲዘምት ትእዛዝ ቢሰጠው እሺ የሚል የመከላከያና የፖሊስ ሃይል እንደማይኖር ሲረዳ ከመንግስታዊ መወቅሩ ውጭ፣  መለስ ከቅርብ የጎጥ ጓደኞቹ ጋር የሚያዝበት በአንድ ዘር አባላት ብቻ የተሞላና የሚመራ የአፋኝና የገዳይ ቡድን አቁሞ በዘረኛ ቅስቀሳው ማሰለፍ የቻለውን ጥቂት የትግራይ ተወላጆች በሰላይነትና በጠቋሚነት፣ ገንዘብ ያላቸውንም የጭነት መኪናቸውን ሳይቀር ለእስረኛ ማመላለሻ እንዲያቀርቡ አድርጎ በዘር የተደራጀ የአፈና የጭፍጨፋ ስራ ሰርቶ ሌላውን ወገን በዘር ጥላቻና በኢንተር ሃምወይነት ለመክሰስ እፍረት የማይሰማው አደገኛ ፍጥረት ነው፡፡

መሳፍንቶቹንና ደርጎቹን በሸዎች ያሰከነዳ ዘረፋ እያካሄደ፤ « ለጤነኛ የኢኮኖሚ እድገት ሲባል መንግስትና ወያኔ ከነጋዴነትና ከቸርቻሪነት ይውጡ » የሚሉትን ሃገር ሊዘርፉ የሚፈልጉ ብሎ መክሰስ ለመለስ ዜናዊ አይኮሰኩሰውም፡፡ የዋጋ ግሽበት ከመቶ ፐርሰንት ባለይ በሆነበት ወቅት 20 በመቶ ነው ብሎ መዋሸት፤ የታወቁ የአለም ድርጅቶች «የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ 5 በመቶ ማደጉንም እንጠራጠራለን»  ሲሉ «12 በመቶ እያደገ ነው ብሎ ማለዛን፣ የታራቡት ቁጥር 12 ሚሊዮን ነው ሲባል የለም 4 ሚሊዮን ነው፣ መለስ ብሎ 6 ሚሊዮን ሆኗል፤ መለስ ብሎ ደግሞ አዎን ርዳታ የሚያስፈልገው 12 ሚሊዮን ነው» ማለት ለመስ ዜናዊ ቸግር ያለበት ጉዳይ አይደለም፡፡

«የአለማችን የኢኮኖሚ ቀውስ እኛን አይመለከተንም፣ የሚመለከታቸው የፋይናንስ መርከባቸው ከታላቁ ውቅያኖስ ውስጥ ገብቶ እንዲቀዝፍ ያደረጉትን መንግስታት ነው፡፡ የእኛ የኢኮኖሚ ጀልባ የታሰረችው ትንሽ ወንዝ ዳር ስለሆነ በማእበሉ አትነካም» በማለት በህጻናት ማሳደጊያ ቋንቋ ለፓርላማው ጥራዝ ነጠቅ የኢኮኖሚ ትንተናውን እንዳላቀረበ ሁሉ፤ መለስ ብሎ «ምአራብ መንግስታት ካልረዱን ማለቃችን ነው» ለማለት መለስ አይቀፈውም፡፡ ከ30 በመቶ ባላይ አመታዊ በጀቱን ከምእራብ መንግስታት በልመና የሚያገኝ አገዛዝ፣ በእዚህም የተነሳ የመለስ አገዛዝ እውነተኛ የፖለቲካ ልኡላዊነት የሌለው መሆኑን ምእራባውያን እያወቁ መለስ ዞር ብሎ ለምእራብ ሚድያ «በአመት መቶ ሽህ የማይሞላ ዶላር ከውጭ እርዳታ የሚያገኙ ለሰብአዊና የሲቪል መብት የሚከራከሩ  ግብረ ሰናይ ድርጅቶች፣ ስራቸውን ለማካሄድ ከ10 በመቶ በላይ በጀታቸውን ከውጭ ማግኘት አይችሉም ያልነው የፖለቲካ ልኡዋላዊነታችንን ለማስከር ብለን ነው» ይላል፡፡

ፖሊሶች ማንን እንደሚይዙና እንደሚያስሩ፣ ዳኞች በማን ላይ ምን አይነት ፍርድ ማስተላለፍ እንዳለባቸው በትእዛዝ ማስፈጸም እንዲችል አድርጎ ያቆመውን የአፈና ስርአት፤ ነጻ የፍትህ ስርአት አድርጎ ሲያቀርብ፤ ማንኛወም የፖለቲካ እስረኛ በነጻ ፍርድቤት በተከናወነ የፍትህ ሂደት ብይን አግኝቶ ለእስር የሚዳረግ መሆኑን አይኑንን አፍጥጦ፣ ያውም በአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን፣ በአለም ህዝብ ፊት ሲናገር መለስ ዜናዊ የህሊና ጉንተላ የሚባል ነገር ፊቱ ላይ አይነበብም፡፡

«ያቆምከው ስርአት በዘር ላይ የተመሰረተ ጥቅምና ስልጣን ያከፋፍላል፡፡ ይህንንም ቁልፍ የሆኑትን የሲቪልና የወታደራዊ ተቋማት ከገዛ ጎጥህ በመጡ ግለሰቦች እንዳስዝያክ፣  ለከፍተኛ ትምህርት እድል እነማን ወደ ውጭ እንደምትልክ ፣ በአንተ የስልጣን ዘመን እነማን እንደከበሩ በማጥናት የደረስንበት መደምደመያ ነው» የሚሉትን የገዛ ወዳጆቹን የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት ሰዎች ሪፖርት፣ ሃገሪቱንና ወያኔን በሚጠሉ አክራሪ ኢትዮጵያውያን ግፊት የተቀናበረ ሪፖርት ነው ለማለት መለስ አይጨንቀውም፡፡ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ ሂዩማን ራይት ዎች፣ ጀኖሳይድ ዎች በአንድ ላይ በአንድ ድምጽ «ህዝብ  ትገላለህ፣ በግፍ ታንገላታላህ፣ ከቀየው ታፈናቅላለህ፣ ለስደት ትዳርጋለህ፣ መንደር ታቃጥላለህ፣ ሴት ልጆችን በአባታቸው ፊት፣ ሚስቶችን በባሎቻቸው፣ እናቶችን በልጆቻቸው፣ አሮጊቶችን የልጅ ልጆቻቸው በሚሆኑ ወታደሮችህ ታስደፈርላህ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ታዋከባለህ፣ እንዳይንቀሳቀሱ ታደርጋለህ» ብለው የሚያቀርቡብኝ ክስ «በጥላቻ የተሞላ፣ ከየስደተኛ ጣቢያው፣ ማንንም እየጠየቁ የሚፈበርኩት ነው» በማለት መለስ ከልቡ ሲናገር ለተመለከተ «እውን ይህ ሰውዬ ውሸትን ለታክቲክ ሲል ከሚጠቀምበት ደረጃ በላይ አልፎ፣ ውሸቱን እውነት ሆኗል ብሎ ከሚያምንበት ደረጃ ላይ ደርሷልን?» የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሰሞኑን መለስ ዜናዊ ከበቢሲ ጋዜጠኛ ከዘይነብ ባዳዊ ጋር ባደረገው ወይይት የታዘብነው ይህንን ነው፡፡ ጋዜጠኛዋ ደግማ ደጋግማ ሂዩማን ራይት ዎች ያቀረበውን የሰብአዊና የፖለቲካ መብቶች ጥሰት ዘገባ እየጠቀሰጭ ላቀረበችለት ጥያቄ መለስ ዜናዊ ያለምንም ሃፍረት እየደጋገመ ሂዩማን ራይት ዎች ይዋሻል እያለ ሲደነፋ ሰምተነዋል፡፡ በእዚሁ የቢቢሲ ቃለ መጠይቅ ጋዜጠኛዋ የረሳችውን በቅርቡ ጀኖሳይድ ዎች በዘር ማጥፋት ወንጀል መለስ እንዲከሰስ ስለጻፈው ደብዳቤ ጠይቃው ቢሆን ኖሮ ወዲ ዜናዊ ድርቅ ብሎ « ባደረግነው ማጣራት የሞቱት በሙሉ መንግስቴን ለማስጠላት ብለው የራሳቸውን ህይወት በገዛ እጃቸው ያጠፉ መሆናቸውን ደርሰንበታል» ለማለት እንደማይመለስ ጥርጥር አልነበረውም፡፡

የሚደንቀው ነገር መለስ ዜናዊ «ታላላቆቹ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሚጋች ድርጀቶች  «ውሸት ይፈበርኩብኛል» እያለ ማንም ተአማኝነት የማይሰጠውን ቅጥፈት ለቢቢሲ ጋዜጠኛ ያለምንም ይሉኝታ ሲተርት የራሱን ውሸታምነት የሚያጋልጥ ድርጊት እየፈጸመ እንደነበር መረዳት አለመቻሉ ነው ፡፡ መለስ ዜናዊ ውሸትን ለብልጣብልጥነት ብቻ ሳይሆን እውነት አድርጎ ማየት የጀመረ ህሊና ከተላበሰ ሰንብቷል፡፡ ይህ ደግሞ መሞቻቸው የደረሰን  ገዥዎች የሚጠናወት መድሃኒት የሌለው በሽታ ነው፡፡ በእዚህ በሽታ የተለከፉ ግለሰቦችና ድርጅቶች እጅግ አደገኞች ናቸው፡፡ በመሆኑም ወልዶ ያሳደጋቸው ውሸት ገዳያቸው እንደሆነ ብናውቅም፣ ውሸታቸው ከሚፈጥረው አደጋ ራሳችንን ተካላክለን፣  እነዚህ ግለሰቦች በእዚህ የታመመ ህሊናቸው እየተመሩ እስከ አሁን ባሀገራችንና በሁላችንም ላይ ካደረሱት ጥፋት በላይ ተጨማሪ ጥፋት ሳያደርሱ እድሚያቸውን ማሳጠር የሁሉም ኢትዮጵያዊ የዜግነት ግዴታ ነው፡፡



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

## ሥርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ

ሚያዚያ 2001 ከግንቦት 7 የኢኮኖሚ ሪፖርተር፡ አዲስ አበባ

ተአምረኛው የአቶ መለስ መንግስት በመጋቢት ወር የመጨረሻው ሳምንት አንድ ትልቅ ተአምር አበሰረ፡፡ ማክሰኞ መጋቢት 23 ቀን 94 ቡና ላኪዎች በመጋዘነቸው ያከማቹትን ቡና ወረሰ፡፡ ብቻ በመለስ የሽፍነፍን ቋንቋ ሁሉም ነገር ሽፍንፍን ስለሆነ ወረሰ አልተባለም፡፡ ማለት ነውር ነው፡፡ ቡናው ታገደ ነው ያለው፡፡ ሰራተኛው ከስራ ሲባረር « ከሥራው ተባረረ» ወይም «ተሰናበተ» አይባልም፡፡ ታገደ እንደሚባለው ቡናውም ታገደ፡፡

የሆነውን ነገር በቀጥታ ለመናገር ሀሞት የሌላቸው አቶ መለስ ሁሉን ነገር በተቃራኒው እንደሚያወሩ ማለት ነው፡፡ ኢኮኖሚው ሲወድቅ አደገ አይደል የሚባለው? ህዝብ ሲሰቃይ ተደሰተ፤ሲራብ ጠገበ ነው፡፡ አመዱ ሲወጣ ወዛ ነው፡፡ መናገርና መፃፍ ከልክሎ መብት ሰፋ አደገ ነው፡፡ የሕዝብ ድምፅ ሰርቆ እንከን የሌላው ምርጫ እንደማለት፡፡ በመሆኑም ሁሉን በተቃራኒ መግለጽን የተካነው መለስ ቡናውን ወረስኩ አላለለም፡፡ አገድኩ ነው ያለው፡፡ እናንተም ቡና ማገድ ማለት ምን ማለት ነው ብላችሁ አትጠይቁ፡፡

የአቶ መለስን መንግስት ባህርይ ሳስብ ምን ትዝ እንደሚለኝ ታውቃላችሁ? 1984 በሚል ስም ጆርጅ ኦርዌል የሚባል ጸሀፊ የጻፈው መጽሀፍ ነው፡፡ በዚያ መጽሀፍ ውስጥ መለስን የሚመስል መሪ የሚገዛውን ህዝብ «ጦርነት ሰላም ነው»፡፡ «መኃይምነት ደስታ ነው» ብለው እንዲያምኑ ያስገድዳቸዋል፡፡ ለዚህ ነው ትዝ ያለኝ፡፡ ትዝ ማለቱም አግባብነት አለው፡፡የ 94ቱ የቡና ነጋዴዎች ሲወረስ፤ ስድስቱን ነጋዴዎች ነጥሎ ፈቃዳቸውን ሰረዘ፡፡ ስድስቱ ቡናቸው ተወረሰ፤ፈቃዳቸው ተሰረዘ፡፡ የ 88ቱ ቡናቸው ተወረሰ ፈቃዳቸው ግን አልተነካባቸውም፡፡

ሐሙስ መጋቢት 25 ቀን የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትርና ምክትላቸው የቡና ላኪዎችን ሰብስበው «ጥቂት» የቡና ላኪዎች ቡና በማከማቸት አገሪቱ የወጪ ምንዛሪ እንዳታገኝ አድርገዋል በተባሉ ላኪዎች ላይ የተወሰደውን እርምጃና፤ መንግሥትም ወዶ ሳይሆን ተገዶ እርምጃውን መውሰዱን ለሰብሳቢዎቹ አስረዱ፡፡ ላኪዎቹ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸውም ሚኒስትሮቹ ጠቅሰው ሆኖም ከስህተታቸው ሊታረሙ ባለመቻላቸው፣ እርምጃው በደብዳቤ ተገልጾላቸው መጋዘኖቹ መታሸጋቸውን፣ በስድስት ላኪዎች ላይ የፈቃድ መሰረዝ እርምጃ መወሰዱን ነገሯቸው፡፡

ሰዎቹ የተጠሩት ይህን ለመስማት አልነበረም፡፡ ይህማ ቢሆን ለቀባሪው ማርዳት ይሆን ነበር፡፡ ነጋዴዎቹ የተጠሩት ቡና ወደ ውጭ ሸጠው የውጭ ምንዛሪ ለመንግስት እንዲያስገቡ፤ ይህንን ካላደረጉ ግን በሌሎች ላይ የተወሰደው እርምጃው በነሱም ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆን ለማስፈራራት ነው፡፡ ቡናችሁ ይወረሳል፡፡ ፈቃዳችሁ ይሰረዛል ነው ባጭሩ ያሉት፡፡

እንዲህ አይነቱ እርምጃ የመጀመሪያው አይደለም፡፡ የመጨረሻውም አይሆንም፡፡ የዛሬ ሁለት አመት ገደማ የእህል ዋጋ ለምን ተወደደ ተብለው ሲጠየቁ፤ ተአምረኛው አቶ መለስ ገበሬው ገንዘብ በገንዘብ ስለሆነ እንደ ድሮው ምርቱን እንዳገባ አይሸጥም፡፡ እንደ ድሮው ነጋዴና ደላላ አያወናብደውም፡፡ በገመድ አልባውና በኋላም በሞባይል ስልኮቹ የአገር ውስጥና የውጭ ዋጋ ጠይቆ፤ ተገቢውን ዋጋ ሲያገኝ ብቻ ስለሚሸጥ ነው ብለው መለሱ፡፡ ከዚህ የባሰ ቀልድ በገበሬው ላይ የተቀለደ አይመስለኝም፡፡

በአመቱ ዘንድሮስ ምን ሆኖ ነው የእህል ዋጋ የናረው ሲባሉ የሚቀባጥሩትን የማያጡት መለስ አሻጥረኛው ነጋዴ ነው ጉድ እያደረጋችሁ ያለው፡፡ በየመጋዘናቸው፤ በየወፍጮ ቤቱ እህል አከማችተው ሰው ሰራሽ እጥረት በመፍጠር ዋጋ አንረው እያስራቧችሁ ነው አሉ፡፡ ከዳሚዎቻቸውን (በዘመኑ ቋንቋ ካድሬዎቻቸውን) አዘመቱባቸው፡፡ ለንግድ ያከማቹትን እህልም ወረሱ፡፡ በኋላም የተወረሰው እህል የት እንደገባ ሳይታወቅ «ጠፋ»፡፡
የእህል ዋጋ ከዚያ በኋላ እየባሰበት ሄደ፡፡ የዚህ ዳፋ እሳቸውንና አጫፋሪዎቻችውን ስለማይነካ አቶ መለስ አልተሰማቸውም፡፡

የቡናውም ነገር ይኸው ነው፡፡ ብቻ እንደእህሉ ሳይነካቸው የሚያልፍ አይሆንም፡፡ ድራሻቸውን ማጥፊያ አንድ ሰበብ ነው የሚሆነው፡፡ ለምንና እንዴት ቢሉ እንደሚከተለው ነው፡፡ የታገደው ቡና «ይጠፋል»፡፡ የት እንደገባ፤ ማ እንደወሰደው አይታወቅም፡፡ ግን የቡናው ባለቤትና ቡናው እስከመጨረሻው ላይገናኙ ተለያይተዋል፡፡

**የወያኔ ተአምር የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው፡፡**

አንደኛ፡፡ የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትሩ አቶ ተፈራ ደርበው እና ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ያዕቆብ ያላ ምን አግብቷቸው ነው ይህን መርዶ ለነጋዴዎቹ እንዲነግሩ የታዘዙት፡፡ እነሱስ ምን ብለው ተቀበሉ? የነሱ ኃላፊነት የቡና ምርት የሚያድግበትን ስልት ቀይሰው መተግበር እንጂ ስለ ቡና ንግድ በተለይም ስለማያውቁት የውጭ ንግድ ማን መካሪ፤ ተቆጣጣሪ፤ አስፈራሪ አደረጋቸው? ይህ ጉዳይ ሚመለከተው የውጭ ንግድ ሚኒስትሩን አቶ ግርማ ብሩንና የሥራ ባልደረቦቻቸውን ነበር፡፡ ታድያ እነሱ ሸሽተው ለምን የግብርናዎቹን አጋፈጡ?

እንደሚመስለኝ ብልጡ አቶ ግርም ብሩ <<መለስ>> የወሰደው እርምጃ ትክክል አለመሆኑንና የባሰ ችግር ውስጥ የሚያስገባቸው፤ እንዲሁም አብሮ ከሚሰራው የንግዱ ሕብረተሰብ ጋር ባይፋቀሩም እንደጠላት እንዳያይዋቸው ዘይደው ምስኪኖቹን አቶ ተፈራንና አቶ ያዕቆብን ያጋፈጡ ይመስለኛል፡፡ ግርማ ብሩ የዚህ መንግስት እድሜ ያለቀ መሆኑንና እሳቸውም ከህዝብ ለመወገን፤ ከመለስ ለመራቅ፤ በሕዝብ ጨዋና ተወዳጅ ለመሆን የሚያደርጉት ጥረት አካል መሆኑ ነው፡፡ ብልጡ ግርማ በደርግ ዘመን የመከላከያ ሚስቴር ምክትል ሚኒስትር ሆነው የጦር መሳሪያ ማምረቻው ክፍል ሓላፊ ነበሩ፡፡ ከወያኔ ጋር የተፋቀሩትና ከፍተኛ ባለሥልጣን ሆነው ችግር ሳይደርስባቸው መቀጠላቸው ስለሰውዬው ብዙ ይናገራል፡፡ ተፈራ ቂሉና ያዕቆብ ቂሉ ግን ገና ከመድረሳቸው የነጋዴው ጥርስ ውስጥ ገቡ፡፡

እስቲ አሁን ደግሞ የነጋዴውን ንብረት መውረስና ፈቃድ መሰረዝ የመለስን የውጭ ምንዛሬ ፍላጎት ሊያሟላ ይችላል? የሚለውን ጥያቄ እንመልከት፡፡ ቡና የተወረሰባቸው ነጋዴዎች ወደ ውጭ ከሚላከው ቡና ወደ 80 ከመቶውን የሚሸፍኑ ናቸው ተብሏል፡፡ በጣም ትልልቆች ናቸው ማለት ነው፡፡ እነዚህ ነጋዴዎች አዲስ አበባ ቢቀመጡም ሥራቸው በአገር ውስጥ እስከ ቡና አብቃዩ ገበሬ በውጭ ደግሞ ከዋናዎቹ የቡና አዘጋጅ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ይኖራቸዋል፡፡ በንግዱ አለም የሚፈጠር ሰንሰለት ደግሞ ጠንካራ ነው፡፡ በቀላሉ አይበጠስም፡፡ የነዚህ ሰዎች ደንበኞች የሌላ ሰው ወይም ድርጅት ደንበኛ ቢያንስ በቶሎ አይሆኑም፡፡ ስለዚህም የመለስ ካድሬዎች ቡናውን ቢሰበስቡ በቀላሉ የውጭ ገዢ አያገኙም፡፡

ገበሬውን የሚመለከተውም ቀላል አይሆንም፡፡ ገበሬው የሚያምነው ቡና ገዥ ካልሆነ በስተቀር ለማንም ቡናውን አይሸጥም፡፡ የመተማመኑን ባህርይ ያጠፉትም አቶ መለስ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀደም የቡና ነጋዴዎችና ገበሬዎች ቡና ወደ ወደ ውጭ እንልካለን በሚሉ ነጋዴዎች በደረቅ ቼክ መታለላቸውን በአንድ ስብሰባ ላይ ለአቶ መለስ ቢነግሯቸውም አቶ መለስ ጆሮ ዳባ ልበስ አሉ፡፡

አሁን የአገር ውስጦቹ ገበሬ፤ የአገር ውስጥ ነጋዴና የውጭ ላኪ ነጋዴ አስተማማኝ ሥርዓት በፈጠሩበት ጊዜ ያንን ስርዓት ማፍረስ ማለት በአገር ውስጥ ቡና በአደባባይ እንዳይሸጥ መከልከል ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ከአምራች አካባቢዎች ወደመሐል አገር የሚመጣ ቡና ይቀንሳል፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትሸጠው ቡና ብዛት በእጅጉ ይቀንሳል፡፡ወደ ውጭ የሚሸጠው ቡና ቀነሰ ማለት የቡና ምርት ቀነሰ ማለት አይደለም፡፡ ምርቱ ከአምራቹ እስከተጠቃሚው የተዘረጋውን ይፋ ጎዳና ተከትሎ አይሄድም ማለት እንጂ፡፡

ታድያ የተመረተው ቡና የት ይገባል? ማለት ተገቢ ነው፡፡ ባጭሩ የተወሰነ ቡና ላገር ውስጥ ገበያ ይውላል፡፡ አብዛኛው ግን ድንበር አቋርጦ ወደ ጎረቤት አገሮች ይፈሳል፡፡ የኢትዮጵያን ቡና ለአለም ገበያ የምታቀርበው ኢትዮጵያ ሳትሆን በደቡብ ኬንያ፤ በምስራቅ ሶማሌና ጂቡቲ በምእራብ ሱዳን ይሆናሉ፡፡

እነ መለስ ታድያ ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ ከዳሚዎቻቸውን (ካድሬዎቻቸውን ) ልከው ገበሬውን አስገድደውም፤ ቀምተውም ቢሆን ወደ ውጭ እንዲሸጥ ትእዛዝ ይሰጣሉ፡፡ ይህም አይሳካም፡፡ ታድያ የአቶ መለስ የሰሞኑ ተግባር ውጤቱ ምንድነው ? የዚህ መዘዝ ቀላል አይሆንም፡፡ አቶ መለስ ሳያውቁት እራሳቸውን ለችግር ዳርገዋል፡፡ የሚከሰተውን የሂደት ሰንሰለት እንይ፡፡

በመጀመሪያ ቡና ላኪዎቹ ይጎዳሉ፡፡ ንብረታቸው በመወረሱና ከስራ ውጭ በመደረጋቸው፡፡ ሁለተኛ በዚህ ስራ የተሰማሩ ሰራተኞች ይጎዳሉ፡፡ ከስራ ስለሚባረሩ፡፡ ሶስተኛ ለነዚህ ነጋዴዎች ገንዘብ ያበደሩ ተቋማትም ይከስራሉ፡፡ ብድሩን እስከነወለዱ የሚከፍላቸው ስለሌለ፡፡ አራተኛ አገሪትዋ ልታገኝ የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ አታገኝም፡፡ በዚህም መለስና ጭፍሮቹ ወደ ውጭ የሚያሸሹት የውጭ ምንዛሪ ያጣሉ፡፡ ይህም በመካከላቸው ቅሬታን ይፈጥራል፡፡ እርስበርስም መበላላት ይጀምራሉ፡፡ አምስተኛ መንግስት በግብር፤ በቀረጥና በሱር ታክስ የሚሰበስበው ገቢ ይነጥፋል፡፡ መለስ ለወታደሩ የሚከፍለው ገንዘብ ሲቸግረው ብሔራዊ ባንክ ያለውን ገንዘብ አውጥቶ ይከፍላል፡፡

ስድስተኛ ምርት በሌለበት እየበዛ የሚሄድ ገንዘብ የመግዛት አቅሙ እየወደቀ ይሄዳል፡፡ ዛሬ በአንድ ብር የሚገዛውን ዳቦ ከአንድ አመት በኋላ ለመግዛት ብር በጋሪ ጭኖ መሄድ ሳያስፈልግ አይቀርም ነበር፡፡ «ነበር» ያልኩት ይህ ሳይደርስ የመለስ መንግስት በህዝብ ግፊትና በራሱ ደደብነት በማሰው ጉድጓድ ውስጥ ስለሚቀበር ብቻ ነው፡፡ በዚምባብዌ ሕዝብ የሳቃችሁ ይብላኝላችሁ ማለት ነው፡፡

ይህ ነው እንግዲህ የአቶ መለስ እውቀት ውጤት፡፡ መለስ ሳያውቀው መቀበሪያውን ጉድጓድ መቆፈር ብቻ ሳይሆን የመቀበሪያውንም ጊዜ እያሳጠረ መሆኑን አያውቀውም፡፡ ሲደርስበት እንደልማዱ ይደነባበራል፡፡ ማጣፊያው ሲጠፋው ያጠፋል፡፡ እራሱም ይጠፋል፡፡ የአማራው ተረት የሰለቸው መለስ በማሻሻል « በርበሬ መጣ ሥርገኛ ቀንጥሱ» ይላል፡

## መለስ ዜናዊ በሚቀጥለው የይስሙላ ምርጫ .....

(ከገፅ 1 የዞርር)

ታዛቢዎች መለስ የፓርቲው መሪዎች በእዚህ ጉዳይ እንዲሰበሰቡ እና ከሱ ሌላ ሰው እንደሌለ እንዲነግሩት የፈለገው ካለልክ እየተወጠረ የሚያስቸግረው የእኔነት ስሜቱ ነው ብለዋል። በተጨማሪም ፓርቲው ስለጠየቀው እንጂ እሱ መልቀቅ እንደሚፈልግ ለማሳየት እና ተፈላጊነት ከማጣት ከሚመጣው የስነልቦና ቀውስ ለመሸሽ ሳይሆን አይቀርም ተብሏል። ሁኔታውን በቅርበት የሚከታተሉ የፖለቲካ ተንታኞች መለስ በምንም ተአምር ማንቁርቱን ተይዞ ከስልጣን ካልተወገደ በቀር እንኳን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ይቅር እና ለገዛ ጓደኞቹም እንደማይሰጥ ምንም አያጠራጥርም ተብሏል።

መንግስቱ ሀይለማርያም ለኢህዴሪ ፕሬዝዳንትነት ሲወዳደር አብሮት ቀርቦ የነበረ አንድ የኢሰፓ ባለስልጣን የይስሙላው ምርጫ ሊደረግ ጥቂት ጊዜ ሲቀረው "ከጓድ ሊቀመንበር ጋር እጩ ሆኜ መወዳድ ያሳፍረኛል፤ እሳቸው ለአብዮቱ የከፈሉት መስዋእትነት፤ የሚሰጡት በሳል እና ቆራጥ አመራርን ከእኔ ብቃት ጋር ሳስተያየው የመሬት እና ሰማይ ሆነብኝ፤ እናም በፈቃዴ እራሴን አግልያለሁ" በማለት ተሰናብተው እንደነበር የሚያስታውሱ ታዛቢዎች ዛሬም እነበረከት ተመሳሳይ ድራማ ለመስራት እየባዘኑ እንደሆነ ለመገመት እንደማያዳግት ይናገራሉ።

መለስ ዜናዊ በውጪ ጋዜጠኞች ለአስራ ዘጠኝ አመት የሙጥኝ ያለውን ስልጣን መቼ እንደሚለቅ በተደጋጋሚ ተጠይቆ "በእኔ በኩል በቅቶኛል፤ ከዚህ ዞር በኋላ ባልቀጥል እመርጣለሁ፤ ፓርቲዬ ቆይ ካለኝ ግን እቀጥላለሁ" ብሎ እንደነበር ይታወሳል።\

## ወያኔ በመጪው ምርጫ አጃቢ ለማግኘት... ....

(ከገፅ 1 የዞረ)

የግንቦት 7 ድምጽ ባቅርብ ስርጭቱ የመለስ ዜናዊን በስብሰባ ወቅት ምርጫ 97 ላይ የታየው ሽንፈት እስከዛሬ ከውስጣቸው ያልወጣላቸው አንዳንድ የአመራሩ አባልት በስትራቴጂው ወጤታማነት ላይ ያላቸውን ስጋት በመዘርዘር ከማንኛውም ተቃዋሚ ፓርቲ ጋር የአደባባይ ክርክር ማካሄድ ያለፈውን አይነት ያልተጠበቀ ቅሌት ሊያስከትል እንደሚችል ስጋታቸውን ደጋግሞ ሲገልጹ እንደነበር ተያይዞ የደረሰን መረጃ ያመልክታል:: ነገር ግን እራሳቸው በሚፈጥሩት የማደናገሪያ ስልት እራሳቸውን አሳምነው ሌላውም ይከተለናል ብለው የሚያስቡ እንደመለስ ዜናዊና በረከት ስምኦን አይነቶቹ የጅል ጮሌዎች: "ተቃዋሚዎችን ያላሳተፈ ምርጫ ማካሄድ አለም አቀፍ ተቀባይነታችንን አደጋ ላይ ይጥለዋልና ልንቆጣጠርው በምንችል ስልት ላይ የተቀነባበረ የምርጫ ዘመቻ ማካሄድ አማራጭ የሌለው ገዴታ ነው" በማለት እንደተከራከሩና ይሄው አቋም እንዲጸድቅ ከፍተኛ ጫና እንደፈጠሩ ለመረዳት ተችሎአል::

የግንቦት 7 ድምጽ ብዚያው ስርጭቱ የመለስ ዜናዊን በተደጋጋሚ "ከዚህ ቦኋላ የጠቅላይ ምንስትርነት ስልጣኔን እለቃለሁ" የማለት አቋም ለማስቀየር: አንዳንድ የኢሃደግ ከፍተኛ ባለስልጣናት የተቀነባበረ የውስጥ ለውስጥ ቅስቀሳ ካደረጉ ቦኋላ ከ2002 ቦኋላ ለሚኖረው ሌላ 5 አመት እንዲቀጥል የሚጠይቅ ውሳኔ ማስተላለፋቸውን መዘገቡ ይታወሳል ::

መለስ ዜናዊ ባለፈው ሚያዚያ 1 ቀን በቢቢስ አለም አቀፍ አገልግሎት ሃርድ ቶክ ፕሮግራም በቀረበው ቃለ መጠይቅ ላይ: የሥልጣን ዘመኑ መቼ እንደሚያበቃ የቀረበለትን ጥያቄ አጨናብሮ ለማለፍ የሳየውን ሙከራ: ጠያቂዋ ዘይነብ ባዳዊ በትክክል እንዲመልስ ባሳደረቺበት ትጽዕኖ ከዚህ የአገልግሎት ዘመን ቦኋላ እንደማይቀጥል በተለመደው ቅጥፈቱ ለመናገር መገደዱ ተስተውሎአል:: ብዙ የቅጥፈት ንግግር በተሞላበት በዚህ የሃርድ ቶክ ቃለ ምልልስ ወቅት በጥያቄዎቹ ባህሪይ ምክንያት መለስ ዜናዊ ቆሌው እንደተገፈፈ የተስተዋለ ሲሆን መቼ ሥልጣን ለመልቀቅ እንደሚያስብ የተጠየቀውን ጥያቄ በቀጥታ መመልስ ተስኖት ቃላት ሲያምታታ እንደነበረ ታይቶአል :: አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በ19 አመት የሥልጣን ዘመኑ በርካታ ንጹሃን ዜጎቻችን ያስጨፈጨፈ፣ በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩትን ለእስርና እንግልት የዳረገ፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩትን ከኑሮ ያፈናቀለና ለስደት ያበቃ ፖሊሲ በተግባር ሲያውል የነበረ ለዚህም ወንጀሉ በአለም አቀፍ ፍርድቤት ክስ እንዲመሰረትበት በተለያዩ ገለልተኛ አለም አቀፍ ተቋሞች ጭምር ውትወታ እየተደረገበት ያለ ከዘመናችን ኋላ ቀር አምባገነን ገዥዎች አንዱ ነው::

## መለስ ዜናዊ 5 የጦር ሄሊኮፕተሮችን ...

(ከገፅ 1 የዞረ)

ባለፈው ታህሳስ የግንቦት 7 ድምጽ ወያኔ በዳርፉር አምስት ሺህ ጦር ለማዝመት ቃል ከገባ በኋላ፤ የመጀመሪያዎቹን 107 ወታደሮቹን በምእራብ ዳርፉር ከተማ ኢል ጌኒናአ ማስገባቱን እና በቀጣዮቹ ቀናትም 415 ወታደሮች ማስፈሩን መዘገቡ ይታወሳል። ኩልብስ በተባለች ሌላ የምእራብ ዳርፉር ከተማ 314 ወታደሮች ቀደም ብሎ አስፍሮ የነበረው ወያኔ፤በታህሳስ ተጠቃለው ከገቡት ጋር 860 ጦር እንደሚኖረው የግንቦት 7 ድምጽ ወታደራዊ ምንጮቹን ዋቢ አድርጎ መዘገቡ አይዘነጋም ።

ከጦር ሰራዊቱ ጎን ለጎን የኢትዮድያ ትንሳዔ ፤የኢትዮድያ መካከለኛ ትራንስፓርት እና የተለያዩ እቃ አቅራቢ የተባሉ የወያኔ ኩባንያዎች 545 ሰራተኞች ይዘው በባለፈው ታህሳስ መጨረሻ ዳርፉር እንደገቡ ይታወቃል። ወያኔ የዲፕሎማሲ ትርፍ አገኝበታለሁ ከሚል ከንቱ ስሌት ወታደሩን ለእሳት መማገዱን አጧጧፎ መቀጠሉ እና በጎረቤት ሀገራት ሳይቀር የቢዝነስ ኢምፓየሩን እያሰፋ እንደመጣ መዘገቡ ይታወሳል።

## ታዋቂው የአሜሪካን አገር መጽሄት ኒውስ ዊክ የመለስ

(ከገፅ 1 የዞረ)

የወያኔ ወታደሮች ከሶማሊያ ለቀው ቢወጡም፣ ጥለውት የወጡት አገር ግን ከታች እስከ ላይ መከራን መቅመሱን እና 3.4 ሚሊዮን ወይም 40 በመቶ የሚሆነው የሶማሊያ ህዝብ ከቤቱ መፈናቀሉንም ዘግቧል።ከዚህ ሁሉ የንብረት ውድመት እና የደም መፋሰስ በኋላ ዋናው ሽብርተኞችን የማስወገዱ ግብ ካለመመታቱም ባሻገር ረሰል ሃዋርድ የተባሉ ጡረተኛ የአሜሪካ ጦር ጀነራል እንደሚሉት ይህ የወያኔ ዘመቻ ጽንፈኞቹን የባሰ አበረታቷቸዋል።

እነዚህ የወያኔ ውድቀቶችና እየጨመረ ያለው አፈናው አሜሪካ ቆም ብላ ግንኙነቷን እንድታጤን ሊያደርጋት ይገባል የሚለው ይህ ጽሁፍ፣ የአባማ አስተዳደር ለኢትዮጵያ መከላከያ የሚያደርገውን ድጋፍ እና የጦር እቃ ሽያጭ ከሰብዓዊ መብት አከባበር ጋር በማያያዝ መለስ ባህሪውን እንዲያስተካክል ግፊት ማድረግ ይችላል ሲል መክሯል። አሜሪካ የኢትዮጵያው አገዛዝ አፈናውን እንዲያቆም ግፊት ብታደርግበት እንደ ብርቱካን ሚደቅሳ ያሉት የፖለቲካ እስረኞች ብቻ ሳይሆኑ፣ በአፍሪካ ቀንድ ያሉ አፍሪካውያን ሁሉ እና አሜሪካም እራሷ ሊጠቀሙ ይችላሉ ሲል ጥሪውን ቋጭቷል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ** እና **በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን።**

g7radio@ginbot7.org